የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፹፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9[th] Year No. 81
ADDIS ABABA 18[th] July 2003

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፰/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ተሻሽሎ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...................................... ገጽ ፪ሺ፫፻፳፪

## CONTENTS

Coumcils of Ministrs Regualtion No 88/2003

The revised Regulation on the importation of goods on franco-Valuta basis Council of Ministers Regulation ........................................... Page 2322

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፰/፲፱፻፺፭ ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ተሻሽሎ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡ ዕቃዎች ተሻሽሎ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፰/፲፱፻፺፭ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ዕቃዎች</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉት የሚከተሉት ዕቃዎች ብቻ ናቸው።

፩) የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚሲዮኖች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የዕርዳታ ድርጅቶች ለታወቁ አገልግሎቶች የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣

፪) የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚሲዮኖች፣ የአለም አቀፍ ድርጅቶችና የዕርዳታ ድርጅቶች ሹማምንቶችና ሠራተኞች ለግልና ለቤት ውስጥ መገልገያ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO 88/2003 THE REVISED REGULATIONS ON THE IMPORTATION OF GOODS ON FRANCO-VALUTA BAIS CLOUNCIL OF MINISTER REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to articles 5 of the Definition of powers and duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995.

1. *Short title*

This Regulation may be cited as "The revised Regulation on the importation of goods on franco-Valuta basis Council of Ministers Regulation No 88/2003".

2. *Goods that may be imported on Franco-Valuta basis*

Without Prejudice to article 3(2) of this Regulation it is only the following goods may be imported on frnaco-valuta basis.

(1) All goods imported for official use of diplomatic and consular missions, international organizations and donor agencies.

(2) Goods imported for personal and house hold uses of officers and employees of diplomatic and consular missions, international organizations and donor agencies.



ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫) የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች፣ የሲቪል ማኅበራት በስጦታ፣ በዕርዳታ ወይም በልገሳ የሚያስገቧቸው ከሥራቸው ጋር የተያያዘ ለተግባራቸው አጋዥ ዕቃዎች፣

፬) የሃይማኖት፣ የትምህርት፣ የሕክምና ወይም የሞያ ተቋማት ወይም ድርጅቶች ለተቋሞቹ ወይም ለድርጅቶቹ ተግባራት ብቻ የታቀዱ በስጦታ ወይም በዕርዳታ ከውጭ አገር የሚያስገቧቸው ለንግድ የማይውሉ ዕቃዎች፣

፭) ለቤተሰብ፣ ለዘመድና ለጓደኛ ከውጭ አገር በስጦታና በልገሳ የሚገቡ ለንግድ የማይውሉ ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች፣

፮) በማንኛውም መስክ ላለ ተመራማሪ አግባብ ካለው አካል ማስረጃ የሚያቀርብ፣ ከምርምር ሥራው ጋር የተያያዘ በስጦታና በልገሳ የሚገቡ መሣሪያዎች፣

፯) በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ ግለሰቦች የሚያስገቧቸው ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች፣

፰) በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው ጠቅለለው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች የሚያስገቧቸው የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች እንዲሁም ለግል ሥራቸው የሚያውሏቸውና የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች፣

፱) አግባብ ባለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙ በውጭ አገር በዘላቂነት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና የውጭ ዜግነት ያላቸው የኢትዮጵያ ተወላጅ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ሥራቸው የሚሆን የካፒታል ዕቃ፣ ጥሬ ዕቃ እስከ ኮሚሽኒንግ ደረጃ የሚበቃ እና ለግል መገልገያ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣

፲) በስፖርት በኪነትና በመሳሰሉት ለግለሰቦችና ድርጅቶች የሚላኩ ሽልማቶች፣ ለሽያጭ ያልመጡ ለስጦታ ብቻ የሚውሉ ዋንጫዎች ሜዳሊያዎች እና ሌሎች ሽልማቶች፣

፲፩) ወደ ውጭ አገር ለሚላኩ ዕቃዎች በግብአትነት የሚያገለግሉ ዕቃዎች እንደ መለያ፣ ዘሮች እንዲሁም መጠቅለያዎችና እና መያዣዎች የመሳሰሉ፣

፲፪) ለሽያጭ ያልመጡ ስጦታዎች፣ የንግድ ናሙናዎች እና የማስታወቂያ ዕቃዎች፣

፲፫) አገር ውስጥ ገብተው የማይቆዩ በተደጋጋሚ ዕቃ የሚመጣባቸው ኮንቴነሮች፣ ሳጥኖች፣ ጣሳዎች፣ ጠርሙሶች፣ ማድጋዎች እና ሌሎች መያዣዎች፣

፲፬) ለአካል ጉዳተኞች የሚመጡ ወይም የሚላኩ ለንግድ የማይውሉ ዕቃዎችና መሣሪያዎች፣

፲፭) የጐደሉ ወይም ብልሽት ያለባቸውን ዕቃዎች ለመተካት አቅራቢው ከአስመጪው ጋር ባለው የዋስትና ስምምነት መሠረት የሚገቡ ዕቃዎች፣

፲፮) ለአንድ ተቋም መደበኛ ሥራ እና ለግለሰብ ጤና እጅግ አስፈላጊ የሆኑ በአፋጣኝ ሊገቡ ካልቻሉ ሥራው ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ ወይም ሕይወትን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ዕቃዎች፣

፲፯) መንገደኞች ይዘዋቸው የሚመጡት የግል መገልገያዎች፣

፲፰) በጊዜያዊነት ወደ አገር ገብተው ተመልሰው የሚወጡ ዕቃዎች።

(3) Any goods imported by budgeted Ethiopian Government institutions and civic associations related to and supporting their function that are received from abroad as gift, aid and donation;

(4) Goods imported from abroad as gift or donation that are intended solely and exclusively for religious, education, medical or Professional organizations and institutions not to be offered for sale;

(5) Personal and house hold goods excluding motor vehicls imported from abroad as gift and donation for family relatives and friend;

(6) Goods imported as gift or donation to a researcher in any field related to his research activity and who can provide evidence from the appropriate organ;

(7) Personal and house hold effects, excluding motor vehicles, imported by persons upon first arrival to take up residence in Ethiopia.

(8) Personal and house hold effects as well as goods and equipment necessary for their livelihood that are imported by Ethiopians and foreign nationals of Ethiopia orgin who have stayed abroad for various reasons.

(9) Goods imported for investment activities including capital goods and raw materiala adequate up to commissioning stage and for their personal use by Ethiopian and foreign nationals of Ethiopian origin investors who are permanently residing abroad and having license from the appropriate government office;.

(10) Awards obtained by and sent to individuals and organizations for outstanding achievement and cups, medal and other trophies imported for presentation only and not to be offered for sale;

(11) Imported goods used for inputs such as lables, seeds, packages and the like for goods to be exported.

(12) Gifts, trade samples and advertising materials not imported as merchandise;

(13) Repeatedly used containers, boxes, tins, bottles, jars and other packages imported full of any articles liable to a specific rate of duty and being ordinary packages for the goods contained therein;

(14) Goods imported by or sent to individual specialized for use by disabled and handicapped not to offered for sale;

(15) Goods imported for the replacement of short landing or defects accorded by the supplier to the importer under the terms of warranty;

(16) Goods that are extremely vital and urgently needed for the normal operation of an institution or health of a person with out which its function would be obstructed and his survival may be imperilled;

(17) Personal effects imported by travelers;

(18) Goods introduced into the country temporarily and subject to reexport.

፫· <u>የገቢዎች ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

፩· ሚኒስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ያወጣል፤

፪· ሚኒስቴሩ በቂ ምክንያት ሲኖር በልዩ ሁኔታ ዕቃዎች ያለውጭ ምንዛሪ እንዲገቡ ለመፍቀድ ይችላል።

፬· <u>የተሻረ ደንብ</u>

ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር ፰/፲፱፻፹፰ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፭· <u>ቅጣት</u>

ይህንን ደንብ የጣሰ ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል።

፮· <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. *Power of the Ministry of Revenue*
   1. The Minister may issue directive for the implementation of this Regulation.
   2. The Minister may upon sufficient cause in exceptional situations allow goods to be imported on franco-Valuta basis.

4. *Repeal*

The importaiton of goods on franco-Valuta basis council of Ministers Regulation No.8/1996 is hereby repealed.

5. *Penalty*

Any person who violate the provisions of this Regulation shall upon conviction be punished in accordance with the Penal code of Ethiopia.

6. *Effective Date*

This Regulation shall enter in to force as of the 18th day of July, 2003.

Done at Addis Ababa this day of 18th July, 2003.

Meles Zenawi
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Prime Minister

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

**<u>ማረሚያ</u>**

**የአዋጅ ቁጥር 359/1995 የገጽ ቁጥሩ 2216–2221 የተባለው በስህተት ስለሆነ የገጽ ቁጥሩ 2316–2321 ተብሎ ይነበብ።**